# የተሳካ ሚሌኒየም?

ከቀዝቃዛ አየር ጋር ዳምና በዋለችው በጠባቧ ከተማ አመሻሹ ላይ ለነዋሪዎቿ ያልተጠበቀ ክስተት ገጠማቸው። የማርሽ ባንድ በቦታው መኖር ደግሞ ለሰዓቱ ልዩ ግምት ሰጥቶታል። “በሰማይ ላይ የተተኮሱት ርችቶች መጀመሪያ ላይ የፍንዳታ ድምፅ መስሎኝ ነበር ድሪያዬን እንደለበስኩ ስወጣ ግን ከፍንዳታው በኋላ ሰማዩ ላይ የሚታዩኝ ርችቶች የሚያምሩ ነበሩ፣ እስኪያልቁ አይቻቸው ገባሁ። ግን ለምን እንደተተኮሱ አላወቅኩም ነበር” ያለችን ከበዓሉ በኋላ የጠየቅናት የሐረር ከተማዋ የ10ኛ ክፍል ተማሪ መቅደስ ብሩ ነበረች።

ይህቺ ዕለት በ1999 ዓ.ም. በሐምሌ ወር መጀመሪያ ላይ የሐረርን 1 ሺህ ዓመት ለማክበር ወደ ክልሉ የመጡትን በውጭ የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሐረሪ ብሔረሰብ ተወላጆችን አቀባበል የተደረገበት ቀን ነበር።

”በተዘጉ መንገዶች ላይ መንቀሳቀስ የተከለከለ ስለነበር ”ይለፍ” በለጠፈውና የግል ጋዜጠኞችን በያዘው መኪና፤ በአስተባባሪዎቹ አማካኝነት ”ጨለንቆ” ከተባለችው ከተማ ጀምሮ የተቀበልናቸውን በትክክል ቁጥሩን ባላስታውስም በስድስት ካቻማሊ (48 ሰው በሚይዝ) መኪና የመጡትን እንግዶች መጨረሻ ለማየት ወደ መናኸሪያው ሳመራ የነበረው ግርግር፣ የናፍቆት ሠላምታ ልውውጥ፣ የእንኳን ደህና መጣችሁ የአበባ ገፀ በረከት፣ የማርሽ ባንድ ሙዚቃ፣ የርችት ፍንዳታ፣ የአካባቢው መብራት መድመቅ፣ የመንግሥትና የግል ጋዜጠኞች ለእንግዶቹ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ የተፈጠረው ውክቢያ፣ እስከዛች ሰዓት ስሜት ያልሰጠኝ የሚሌኒየም በዓል ስሜቴን እንዲነቃቃ አድርጎት ነበር” ሲል በምሥረታዋ የዕድሜ ብዛት አስታካ በዓሉን ለማክበር የመጀመሪያዋ ስለሆነች ሐረር ከተማ ትውስታውን የነገረን በወቅቱ የነበረ ኢትዮጵያዊ የውጭ ጋዜጠኛ ነው።

በጥብቅ የደህንነት ጥበቃ፣ ቁጥጥርና ፍተሻ ስር በወደቀችው የከተማዋ ስታዲየም በተከበረው በዓል ላይ፤ በርካታ የከተማው ህዝብ ተገኝቶ የነበረ ቢሆንም፣ ከዝግጅቱ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር ”ጎዳሴ” የሚለው ቃል በአደራ የተሰጠ ይመስል፣ ወዲያውኑ የመንግሥት መገናኛ ብዙኀን የመቀበላቸው ሁኔታ፤ የከተማው ዋናው መንገዶች በኦራል መኪናና በፌዴራል ፖሊስ ታጥሮ እስከ ማምሻውን ከእንቅስቃሴ ለተገታው የከተማው ነዋሪ የተረፈው ነገር እንዳልነበር በመግለጽ ጋዜጠኛው ትውስታውን ይቀጥላል።

”በመንገዶቹ መዘጋጋት የምሄድበት በማጣቴ፣ ከአንዱ የሐረር ልጅ ጋዜጠኛ ጓደኛችን ቤተሰቦች ቤት በእግራችን መንገድ እያሳበርን ሄድን። ከተማው ፀጥ ረጭ ብሏል። ለማድመቂያ የተሰቀሉት መብራቶች ቀን በመኾኑ ምክንያት ባለመብራታቸው፣ ሐረር ከክብረ በዓሏ ይልቅ ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ ተከስቶ የነበረውን የፀጥታ ድባብ ታስታውሳለች። ወደ ጓደኞችን ዘመድ ቤት ስንገባ፣ ከመግቢያው በር ጀምሮ በድፍርስ ውሃ የተሞሉ በርካታ የውሃ ማጠራቀሚያ ፕላስቲኮች ተደረድረዋል። ከቆይታ በኋላ የባለቤቶቹና የተከራዮቹ ፕላስቲኮቹ በወር አንዴ የሚመጣውን ድፍርስ ውሃ ማጠራቀሚያ መሆኑን ተረዳሁ። የከተማው ነዋሪ ከሆኑ የጓደኛዬ ዘመዶች፤ ስለዲያስፖራዎች አቀባበል፤ ስለርችቱ፤ ስለማርሽ ባንድ፤ ስለስታዲየሙ፣ … በአጠቃላይ ስለዝግጅቱ፣ ሲሆን ከሚያዩት በስተቀር በከተማዋ ምን እየተደረገ እንዳለ የሚያውቁት እንደሌለ አጫወቱኝ፤ ”አቦ ግርግሩን ትተው በዓሉን አስታከው የውሃ ችግራችንን ቢቀርፉልን ጥሩ ነበር” የሚል አስተያየት ስሰማ፣ በደማቁ የዲያስፖራ አቀባበል ሥርዓት ተነሳስቶ የነበረው የሚሌኒየም በዓል ስሜቴ ሲከስም ታወቀኝ” ነበር ያለን በሚሌኒየሙ ማነቃቂያ ሐረር ከተማ ተገኝቶ የነበረው ጋዜጠኛ።

## የኢትዮ ሚሌኒየም በዓል አከባበር ብሔራዊ ምክር ቤት መቋቋም

የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል አከባበር ብሔራዊ ምክር ቤት፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 117/97 መሠረት በአዋጅ ተቋቋመ። ይኼ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሆኖ፤ ፕሬዚዳንቱ፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩና የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስትር አቶ አዲሱ ለገሰ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ስዩም መስፍን እንዲሁም የክልል ፕሬዚዳንቶቹን ጨምሮ ከፍተኛ የሀገሪቱ ባለሥልጣናት የካቲት 29 ቀን 1999 ዓ.ም. በሒልተን ሆቴል ሲሰበሰቡ ከሀገሪቱ መሪዎች ታላቅ ነገር ተጠብቆ ነበር።

የበዓል አከባበር ምክር ቤቱ፣ በዋና ዳይሬክተሩ ለሚመራው የጽ/ቤት ሠራተኞች ታህሣሥ 4 ቀን 1999 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ ላይ የተቋቋመበትን የሁለት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድና የድርጊት መርኀ ግብር አቅርቦ ካፀደቀ በኋላ በማርሽ ባንድ አጅቦ፣ ዓርማውን ሲያስመርቅ የነበረው የሒልተን ሆቴል ሽር ጉድ ለብሔራዊ ምክር ቤቱ ቀጣይ የሥራ አፈፃፀም ግርማ ሞገስ ሰጥቶት ነበር።

## አራቱ ዓላማዎችና አራቱ ምክር ቤቶች

ምክር ቤቱ ያፀደቀው ስትራቴጂክ ዕቅድ አራት ዓላማዎች ነበሩት፡-

አንደኛ፡- መላው ኅብረተሰብ በልማትና በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ረገድ፣ የጋራ ሀገራዊ አመለካከት በመገንባት የተሻለ ገጽታ ያላት ኢትዮጵያን ለማየት ብሩህ ተስፋ ሰንቆ፣ ወደ አዲሱ የኢትዮጵያ ሚሌኒየም እንዲሸጋገር ማስቻል፤

ሁለተኛ፡- ኅብረተሰቡን በልማትና በመልካም አስተዳደር ሀገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ በማንቀሳቀስ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር ማስቻል፤

ሦስተኛ፡- በመንግሥትና በህዝቦች ሙሉ ተሳትፎ የሀገሪቱን መልካም ገጽታ ሊገነቡ የሚችሉ ብሔራዊ እሴቶቻችን ለመላው ዓለም በማስተዋወቅ ሀገሪቱን በኢንቨስትመንት፣ በቱሪዝም፣ በንግድና በሌሎች መስኮች ተመራጭነት የሚያሰጣት መልካም ገጽታን እንዲገነባ ማስቻል፤

አራተኛ፡- ለመላው ኅብረተሰብ፣ ለወጣቱ ትውልድና በአጠቃላይ ለመላው ዓለም ብሔራዊ ዓላማዎቻችንን፣ ተልዕኳችንና የትኩረት አቅጣጫዎቻችንን የሚያመለክቱ ዓበይት መልዕክቶችን ለማስተላለፍ ማስቻል ናቸው።

ይኸን ዓላማ ለማስፈፀም፤ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ የሚቋቋሙ፣ እንደ አስፈላጊነቱ በውጭ ሀገር የሚቋቋሙ ምክር ቤቶች፤ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ብሔራዊ ጽ/ቤት በሚል አራት ምክር ቤት እንዲቋቋሙ ተወስኖ ነበር።

በምክር ቤቱ ጽ/ቤት ለማስፈፀም ከተዋቀሩት 36 (ሠላሳ ስድስት) ፕሮጀክቶች ውስጥ የጽ/ቤቱ የማስፈፀም ብቃትና አቅም አንፃር በጽ/ቤቱ አቅም እውን ማድረግ ይችላሉ በሚል 17 (አሥራ ሰባቱን) አጽድቀው ቀሪዎቹን ደግሞ፤ በተባባሪዎችና በሌሎች ባለ ድርሻ አካላት በተሻለ ሊፈፀሙ የሚችሉ፣ ራሳቸውን ችለው ብቻቸውን እንደ ፕሮጀክት

ከሚሄዱ ይልቅ ከሌሎች ጋር በአንድ ማዕቀፍ ተካትተው እንዲሄዱ ማድረጋቸውን በጽ/ቤቱ ዳይሬክተር አቶ ስዩም በረደድ አማካኝነት በየካቲት ወር 1999 ዓ.ም. የሥራ አስፈፃሚ ስብሰባ ላይ ተገልጾ ወደ ሥራ እንደተሰማሩ ጥቆማ ተሰጠ።

## የምክር ቤቱ የሥራ ጊዜ ተጠናቋል?
## እቅዶቹ የት ገቡ?

የሚሌኒየም በዓል አከባበር ምክር ቤት በአዋጁ የተሰጠውን የሥራ ጊዜ አጠናቆ ጥቅምት 7 ቀን 2001 ዓ.ም. በሼራተን ሆቴል ሥራ አስፈፃሚው በሚያደርገው ስብሰባ ጽ/ቤቱ በይፋ ይዘጋል። (ምናልባትም እንደገና በይፋ ካልተከፈተ ወይም በአዋጅ የሥራ ጊዜ ካልተራዘመለት) የተጠናቀቀውንም የሥራ ጊዜ አስመልክተው፣ የጽ/ቤቱ ዳይሬክተር አቶ ስዩም በረደድ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለፁት፣ በዕቅድ ከተያዙት ፕሮጀክቶች 80 በመቶ ያህል ብሔራዊ መግባባት ለማስፈን፣ ፀረ-ድህነት ትግሉን በድል ለመወጣትና የኢትዮጵያን ኅዳሴ ለማረጋገጥ የሚያስችል መነቃቃትን በመፍጠር ተጠናቋል ሲሉ ገልፀዋል።

የጽ/ቤቱ የሰው ኃይልና የቁሳቁስ ማስተባበሪያ ዘርፍ ቡድንመሪ ዶ/ር ዮሐንስ ገ/ስላሴ ለእንቢልታ ሲገልፁ፣ የበዓል አከባበር ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን በመስከረም ወር 2001 ዓ.ም. ሲጠናቀቅ ከ85 በመቶ በላይ ፕሮግራሞቻቸውን ማጠናቀቃቸውን፣ ቀሪዎቹን በሚመለከት እንዴት ይደረጉ? የሚለውን በጥቅምት ሰባት የሚሰበሰበው ሥራ አስፈፃሚ እንደሚወስን ተናግረዋል።

እንደ ዶ/ር ዮሐንስ ገለፃ ከተያዙት 17 (አሥራ ሰባት) እቅዶች፤ "ሁለት ዛፍ ለሁለት ሺህ" 700 ሚሊዮን ዛፎችን በመትከል ተጠናቋል፤ "ሕብር የኛ ሚሌኒየም" በሚሌኒየም አዳራሽ ለዋዜማው በተደረገው ዝግጅት፣ በጃንሜዳና በስታዲየም የሙዚቃ ድግስ ተጠናቋል፣ "የሚሌኒየም ፓርክ" ከአዲስ አበባው የካ ሚሌኒየም ፓርክ ጀምሮ በየክልሉና በየወረዳው ተገንብቷል፣ "መጽሐፍ መለገስ" የተወሰኑ መጻሕፍት ተሰባስበዋል፣ "የክብር መዝገብ" የተወሰኑ የአፍሪካ መሪዎች እንዲፈርሙ ተደርጓል፣ "የአፍሪካ ሣምንት" በአፍሪካ መሪዎች ስብሰባ ላይ ተካሂዷል፣ "ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ውይይት" የሰው ልጅ አፈጣጠር፣ ስለስፖርት፣ ስለቅርስ ማስመለስ፣ ኢትዮጵያ ለሣይንስ ዕድገት ስላበረከተችው አስተዋጽዖ ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ተካሂዷል።

"ሁለገብ የወጣቶች ማዕከል" ግንባታ፣ የሦስት ሐውልቶች ግንባታ፣ የቦንጋ ብሔራዊ ሙዚየም ግንባታ፣ በበቆጂ የአትሌቲክስ ሙዚየም ግንባታ፣ በሚል የተያዙ ፕሮጀክቶች አልተጀመሩም ዶ/ር ዮሐንስ በበኩላቸው ግንባታውን ባለው ጊዜ ማስጀመር እንደማይቻል በመከራከር "የወጣቶችን ማዕከል ለመገንባት ካርታውን እስካሁን አልተረከብንም እንጂ ፍልውሃ አካባቢ ቦታ ተፈቅዶልናል። ለሁሉም ወጣቶች የሚሆን ማዕከል እንዲገነባ የዲዛይን ሥራው ተጠናቋል። ሎተሪ ተሸጦ ከተገኘ ወደ 13 ሚሊዮን የሚሆን ብር ተቆራርጦ 4 ሚሊዮን አካባቢ ደርሶናል ተጨማሪ ፈንድና ስፖንሰር እያፈላለግን ነው" ብለዋል።

የቦንጋ ብሔራዊ ሙዚየም ግንባታን በሚመለከት ሲገልፁም፤ የዲዛይን ሥራው መጠናቀቁንና ወደ 6 ሚሊዮን ብር የሚገመት ገንዘብ መገኘቱን፣ ግንባታው በቅርቡ ይጀመራል ብለው እንደሚገምቱ ገልፀዋል።

በበቆጂ የአትሌቲክስ ሙዚየም ግንባታ ዕቅድ ላይ መሆኑን፣ ሦስቱ ሐውልቶች (የአፍሪካ፣ የሴቶችና፣ የብሔር ብሔረሰቦች) ግንባታ ስፖንሰር የሚያደርጉ ድርጅቶችን ማግኘታቸውንና ግንባታዎቹ ግን አለመጀመራቸውን ገልፀዋል።

የግንባታዎቹ መጠናቀቅ ሲጠበቅ ጭርስኑ አለመጀመር ምክንያት ነው ያሉትን ዶ/ር ዮሐንስ ሲገልፁ፤ ስፖንሰር ሲያፈላልጉና የዲዛይን ሥራውን ሲያሠሩ ጊዜ እንደወሰደባቸው ይናገራሉ።

## የበዓሉ በይፋ መጀመር

በዓሉ መከበር ያለበት በ2001 ዓ.ም. እንደሆነ ተከራካሪ ወገኖች ቢኖሩም፣ መንግሥት በአዋጅ ባፀደቀው መሠረት በይፋ የተጀመረው ግንቦት 28 ቀን 1999 ዓ.ም. ነበር።

የሚሌኒየሙን የዋዜማ በዓል፣ በሚሌኒየም አዳራሽ የከፈቱት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ያደረጉት ንግግር፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ በልቡ ተስፋን እንዲሠንቅ ሊያደርግ የሚችል ማለፊያ ዲስኩር ነበር ሲሉ አስተያየት የሚሰጡ ወገኖች አሉ።

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ፣ በዋዜማ በዓል ንግግራቸው፣ አዲሱ ሚሌኒየም እጅ ለእጅ ተያይዘን ከጨለማ የምንወጣበት ነው በማለት አበሠሩ።

"አዲሱ ሚሌኒየም ለኢትዮጵያውያን አዲስ ምዕራፍ ነው" በማለት ንግግራቸውን የቀጠሉት መለስ፣ ኢትዮጵያውያን የተለያየ መልክ ባለው ልዩነት የሚኖሩና ይህ ልዩነት የችግራችን ምንጭ ሳይሆን የጥንካሬያችን መገለጫ አድርገው፣ በመቻቻልና ሥርዓት ባለው መንገድ የጨለማው ማብቂያ ዘመን ይሆናል ብለው ነበር።

የጨለማው ዘመን አብቅቶ በኢትዮጵያ የኅዳሴ ዘመን ዕውን ይሆናል ያሉት መለስ፣ ይህ ትውልድ በእጁ የገባውንና የያዘውን ተስፋ ሰጪ ግስጋሴ ዘላቂ እንዲሆን ለማድረግ ገና ብዙ መሥራት የሚገቡን ነገሮች አሉም ብለው ነበር።

ኢትዮጵያ አሁን ስለምትገኝበት አስከፊ ድህነት ያለፈውን ትውልድ በንግግራቸው መሐል ለመንቀፍም አልፈለጉም፣ ይልቁንም ነፃነትዋን የጠበቀች ሀገር እንድትሆን ያለፈው ትውልድ ደሙን አፍስሶ ለከፈለው መስዋዕትነትና አድናቆታቸውን ነበር የገለፁት።

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ወቅታዊውን የሀገሪትዋን ኢኮኖሚ በተመለከተው ንግግራቸው፣ ኢኮኖሚያችን ዓመታዊ ዕድገቱ ከ10 በመቶ በላይ ነው፤ በዚህ ዓመታዊ ዕድገታችን የምንቀጥል ከሆነ ኢትዮጵያ በመጪዎቹ 20 ዓመታት ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ተርታ ለማሰለፍ የሰነቅነው ግብ እውን እናደርጋለን፤ ከበርካታ ልፋትና ጥረት በኋላ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲን በመገንባት የሚደረገው ሂደት ተስፋ ሠጪ ነው። ዲሞክራሲን በመጪው ጊዜ ለማለምለም ዋና ማዕከላዊ ነጥባችን ነው ያሉት።

አቶ ሣህሉ ወንድም አገኘሁ የተባሉ፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር ዕለቱን ሲያስታውሱ፤ "አቶ መለስ የሚያደረጉት ንግግር ነገር ያዘለ ስለሚመስለኝ ለወትሮው ባይጥመኝ ያን ዕለት ያደረጉት ግን ከእስረኞቹ መፈታት፣ ከሳቸው

ነፃ ሆኖ መደነስና፣ ከሆይታና ጭፈራው ጋር ተደማምሮ ዛሬን ሳይሆን ሌላን ጥሩ ቀን የመናፈቅ ተስፈኛ ሆኜ ነበር የተለመደው ግርግር መሆኑ የገባኝ ዘግየት ብሎ ነው" ሲሉ ዕለቱን ያስታውሳሉ።

## የምክር ቤቱ ሥራ የተሳካ ነበር?

ዶ/ር ዮሐንስ ውጤታቸውን ሲመዝኑ "የተሳካ" ነበር ይላሉ። ለዚህም በዋናነት የሚጠቅሱት 70 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዶ 700 ሚሊዮን ችግኞችን በመላ ሀገሪቱ ለማስተከል መቻሉንና በህዝብ ዘንድ ግንዛቤና ተነሳሽነት መፈጠሩን ነው።

በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር በተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አፈፃፀም መምሪያ ውስጥ ያሉ አንድ የደን ባለሙያ ስለችግኞቹ ሲገልፁ፤ ቀደም ሲል በነበሩት ጊዜያት በየክልሉ የሚተከሉ ችግኞች ብዛት ተሰባስቦና ተደምሮ በግልጽ የተቀመጠ መረጃ እንደሌለ ገልፀው፤ በሚሌኒየሙ ወደ 700 ሚሊዮን ችግኞች መተከላቸውን፤ መምሪያው ለማወቅ የቻለው ከሚሌኒየም ጽ/ቤት በደረሰው ደብዳቤ መሠረት መሆኑን ገልፀዋል።

የተተከሉትን ችግኞች በሚመለከት በሁሉም አቅጣጫ ክትትል እየተደረገባቸው መሆኑን ዶ/ር ዮሐንስ ቢገልፁም፣ የደን ባለሙያው በዚህ ሃሳብ አይስማሙም። የተተከሉት ችግኞች በርካታ በመሆናቸው ተካዩ ድርጅት፣ ኢንዱስትሪ፣ ማኅበር ወይም ግለሰቦች የቅርብ ክትትል እንደሚያስፈልጋቸው ይናገራሉ፤ ያለበለዚያ መተከል ብቻ በራሱ ዋጋ እንደሌለው ያስረዳሉ።

ባለሙያው በማከልም "የችግኞቹ መተከል ሰውን ያነቃቃል፣ ባለቤት እንዲሆንና በባለቤትነት ስሜት እንዲያስብ ያደርገዋል፣ የደን መመናመንን፣ የአየር መበላሸት ወይም መበከልን ይቀንሳል" ሲሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሥጋታቸውን ይጠቁማሉ፣ ችግኞቹ በደቦ የተተከሉ በመሆናቸው፣ የቦታው ሁኔታ፣ የአየር ጠባይ እና የአተካከል ስልቱ የተጠና መሆን እንደነበረበት ይገልፃሉ። "በእርግጥ በተከላው ወቅት፣ የግብርና ጽ/ቤት ባለሙያዎች እየተገኙ ምክርና ትምህርት ሲሰጡ ነበር። ነገር ግን በሁሉ ቦታም ይህ ሁኔታ ነበር ማለት ይከብደኛል" ብለዋል።

ዶ/ር ዮሐንስ በበኩላቸው፤ ምን ያህል ችግኝ ለምን ያህል ጊዜ፣ የአየር ሁኔታውን ሊያስተካክሉ የሚችሉ ሀገር በቀል ዛፎች መሆናቸው፣ በተለያየ የአየር ጠባይ ምን መተከል እንዳለበት በዩኒቨርሲቲ እና በአካባቢ ጥበቃ በታወቁ ፕሮፌሠሮችና ምሁራን ትምህርት እየተሰጠ ተከላው እንደተካሄደ ይናገራሉ።

የባለሙያው ሌላ ስጋት የክትትል ጉዳይ እንደሆነ በመግለፅ፤ ችግኞቹ በቂ ክትትል ካልተደረገላቸው የመጽደቅ ዕድላቸው አነስተኛ እንደሆነና ክትትሉ ደግሞ በተከለው ሰው አማካኝነት ሊደረግ እንደሚገባ ይገልፃሉ። እሳቸው ለሚሠሩበት መምሪያ ክትትል እንዲደረግ ቢፃፍም እስከ አሁን ከዕቅድ ውጪ በተግባር የተደረገ ነገር እንደሌለ ያስረዳሉ። ሃሳባቸውን ሲያጠቃልሉም ችግኝ ተከላውን "የተሳካ" ነው ለማለት እንደ የዛፎቹ ዓይነት በሚገባ መጽደቅ አለመጽደቃቸውን የመከታተያ በቂ ጊዜ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

## ሲጠበቅ የቀረው ዲያስፖራ (Prodigal Son)

አዲሱን ሚሌኒየም ለማክበር በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና የውጪ ዜጎች ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ፣ የሚለው ወሬ መናኘት የጀመረው ሚሌኒየሙ ሊከበር ገና አንድ ዓመት ከቀረው ጊዜ ጀምሮ ነበር።

ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት እንግዶች ብዛት ከሚገባው በላይ ተጋኖ በመቅረቡ የተነሳ፣ በተለይ በአዲስ አበባ ከዚህ በፊት ታይተው የማይታወቁ ክስተቶች ተስተውለዋል።

የቤት አከራዮች የብዙ ጊዜ ተከራዮቻቸውን ከቤታቸው በማስወጣት፣ ለሚመጡት እንግዶች ማረፊያነት ለማከራየት ደፋ ቀና ማለትም የጀመሩት ከዚሁ ጊዜ አንስቶ ነበር።

በንግድ ሥራ የተሠማሩ የንግድ ባለቤቶች ሆቴሎቻቸውን፣ ክለቦቻቸውን እና ሬስቶራንቶቻቸውን ማሳደስና ማስፋፋት የጀመሩት ለዚሁ የሚሌኒየም በዓል አከባበር ወደ ኢትዮጵያ ሥፍር ቁጥር የሌለው "ዲያስፖራ" ይመጣል ብለው ነው።

አንዳንድ ሥራ ፈጣሪዎችም በአዲሱ የቢዝነስ ፕላናቸው መሠረት ገንዘባቸውን ኢንቨስት ማድረግ ጀምረዋል። የከተማው ሆቴሎችና ማረፊያ ቤቶች መላውን እንግዳ ማስተናገድ ስለማይችል፣ በሱሉልታ ጫካ ላይ በድንኳን ለማሥፈር ዝግጅትም መደረግ ተጀምሯል ተብሏል።

ይህም ሁሉ ሆኖ ግን በሚሌኒየሙ ይመጣል ተብሎ ከተጠበቀው በታች "ዲያስፖራ" በመምጣቱ የታሰበው ነገር ሁሉ ኪሳራ ሆኖ ቁጭ አለ።

ከባንክ ብድር በመውሰድ የኪራይ መኪና የገዛው ደምስ የተባለ የአዲስ አበባ ነዋሪ፣ በብድር የገዛውን መኪና የሚከራይለት ዲያስፖራ ማግኘት አልቻለም በማለት ሣምንታዊው ፎርቹን ጋዜጣ በወቅቱ ጉዳዩን (Sail waiting for the prodigal son) በሚል ርዕስ በሰፊው አስነብቧል።

ከአዋሽ ባንክ 300,000 ሺ ብር ተበድሮ የሚከራይ መኪና የገዛው የ28 ዓመቱ ደምስ መኪናውን የሚከራይለት ቢያገኝም፣ የባንክ ብድር ወለድ ግን መጨመሩን አላቋረጠም።

ደምስ ለፎርቹን ሲናገር "እኔ የሰማሁት 700 ሺ በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ 100 ሺ ጃማይካውያን ወደ ኢትዮጵያ ለሚሌኒየም በዓል ይመጣሉ የሚለው ነበር" ብሏል።

ደምስን ጨምሮ በርካታ የአዲስ አበባ ነጋዴዎች ብዙ ሺህ ሀብታሞች ወደ ኢትዮጵያ ይመጣሉ ተብሎ በተጋነነ ቁጥር በቀረበው መረጃ ጉድ ሆነዋል።

ለሚሌኒየም በዓል ይመጣሉ የተባሉ እንግዶች አኀዝ ከ300 ሺ እስከ 700 ሺ ድረስ በማጋነን እርስ በርሱ የሚጋጭ መረጃ ከየት እንደመጣ እነዚህ ነጋዴዎች የሚያውቁት ነገር የለም።

ፎርቹን በዚያን ጊዜ ዘገባው፣ የሐምሌ 6 ቀን 2007 አዲስ ዘመን ዕትምን ዋቢ አድርጎ ወደ 10 ሺ የሚቆጠሩ ጎብኚዎች አዲስ አበባ መግባታቸውን አረጋግጧል።

የብሔራዊ ሚሌኒየም ጽ/ቤቱ በተጋነነው ቁጥር እጁ እንደሌለበት በዋናው ኃላፊ አቶ ስዩም በረደድ በኩል ሲያስተባብል፤ ስዩም ለፎርቹን ያረጋገጡት ግን በአንድ ዓመት የሚሌኒየም በዓል አከባበር ወደ 300 ሺ የሚጠጉ ጎብኚዎች ይመጣሉ ሲሉ ተናግረዋል።

"እኔ መጥተዋል የሚል እምነት ነው ያለኝ" የሚሉት ዶ/ር ዮሐንስ "የዲያስፖራውን ቁጥሩን ማወቅ ያስፈልጋል፣ መጀመሪያ ከኢትዮጵያ ውጪ ያሉት እኮ 100 ሚሊዮን አይደሉም የተወሰኑ ናቸው። ሰሜን አሜሪካን ብንወስድ 1.5 ሚሊዮን ነው ያለው፣ አውሮፕላኖቹ ይዘው መምጣት የሚችሉትን ያህል አምጥተዋል። በኢትዮጵያን ኤርላይንስ በአንድ ጊዜ ትኬት እንኳ ወደ 300 ሺ የሚያህሉት መጥተዋል፣ ይኼ ቀላል ቁጥር አይደለም። ከዚህ በፊት ተደርጎ በማይታወቅ ሁኔታ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተከራይቶ በሌላ አውሮፕላን ያመጣበት ሁኔታ ነው። ያ ብቻ አይደለም እዚያም ኾነው ለመምጣት የማይችሉ ከግምት ውስጥ ገብቶ መምጣት ከሚችለው በታች መጣ ብዬ አልገምትም በጣም ብዙ ነው የመጣው" ይላሉ።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በሰኔ 2007 በወጣው መግለጫ ፎርቹን ጋዜጣ ጠቅሶ ዘግቦ እንደነበረው፤ አየር መንገዱ 25 ሺህ መንገደኞችን ወደ ኢትዮጵያ ለማጓጓዝ ማቀዱን፣ ከዚህ በተጨማሪ መንገደኞችን ለማጓጓዝ ይረዳው ዘንድ ሁለት አውሮፕላኖችን መከራየቱን ጠቁሟል።

ከተከራያቸው ሁለት አውሮፕላኖች (ቦይንግ 767-300) 235 መንገደኞችን፣ (ቦይንግ 757-200) ደግሞ 157 መንገደኞች ብቻ ይይዝ እንደነበር የአየር መንገዱ መግለጫ ያስረዳል።

"ብሔራዊ ም/ቤቱ ከተቋቋመበት አንዱ ዓላማ ኅብረተሰቡን በልማትና በመልካም አስተዳደር ሀገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ በማንቀሳቀስ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር ማስቻል" እንደሆነ የገለጹት ዶ/ር ዮሐንስ፤ "ጽ/ቤቱ ብሔራዊ መግባባትና መነቃቃትን ፈጥሯል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ቢኖሩም፤ ቱሪስቶች ወይም ዲያስፓራዎች መጥተው ሀገር ውስጥ ሲያለሙ፣ ሰንደቅ ዓላማችን በብሔር ብሐረሰቦች በዓል ሲከበር ከመደሰት ውጪ ሊከፉ አይችሉም፤ ይህ ደስታቸው ነው ብሔራዊ መግባባት ተፈጠረ የሚያስብለው" ይላሉ።

የሕብረት ም/ሊቀመንበር ዶ/ር መራራ ጉዲና በዚህ ሃሳብ አይስማሙም፤ "ሚሌኒየሙ የአንድ ሰሞን ግርግር ከመሆን ባለፈ መነቃቃት አልፈጠረም። መንግሥትና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ባሳለፍነው አንድ ዓመት ውስጥ የመነጋገሪያ መድረክ አልፈጠሩም፣ ልማትና ኢኮኖሚን ብንመለከት ደግሞ ቀውስ ነው የፈጠረው። ሌላው የምርጫ ሕጎችን፣ የሚዲያ ሕጎች እና ይወጣል ተብሎ የሚጠበቀው የሲቪል ማኅበራት ሕግ ዲሞክራሲውን ወደ ኋላ ወሰደ እንጂ ብሔራዊ መግባባትን ይዞ ይመጣል የሚለው ባዶ ተስፋ ነው" ይላሉ።

የኦፌዴን ሊቀመንበር አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ደግሞ "ሚሌኒየሙ መነቃቃትን ፈጥሯል" ሲሉ ይከራከራሉ። ገበሬዎችን በማነቃቃትና በማስተማር ጥሩ ልማትን ፈጥሯል፤ በቱሪዝም እና በኢንቨስተሮች ሀገር ውስጥ ብዙ ሥራዎች እንዲሠሩ በመደረጉ በልማት በኩል ለውጥ መጥቷል ባይ ናቸው።

"ሀገራዊ መግባባት ተፈጠረ የሚባለው፣ በተወሰኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ሁሉም ዜጎች ስምምነትና እምነት ሲፈጥሩ ነው" የሚሉት የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ናቸው። "ዜጎች የሀገራቸው የሥልጣን ባለቤት ዋና ምንጭ መሆናቸውን ከባቢያዊ ሁኔታ መፍጠር፣ ሀገራዊ ስምምነት ለመፍጠር መሠረታዊ ጉዳይ ነው" ይላሉ። ያለፈውን ዓመት የፖለቲካ ሂደቱን ስንመለከት ግን ምናልባት የሀገሪቷ የፖለቲካ ሁኔታ በአንድ ወገን ተፅዕኖ ስር ያረፈበት፣ በአጠቃላይ የፖለቲካ እንቅስቃሴው ለተቃዋሚ ወገን የጠበበበት አካሄድ ነበር የነበረው። በተቃውሞ ፖለቲካ ላይ የተሰለፈው የፖለቲካ ኃይል ከመድረኩ በተገፋና ከጨዋታ ውጪ በተደረገ ቁጥር፣ የተወሰነው የኅብረተሰብ ክፍል የሀገሩ ባለቤት ያለመሆኑን እንዲያምን የሚያደርግ ሁኔታ ነው የተፈጠረው። ስለዚህ ሀገራዊ መግባባት ከመፍጠር ይልቅ ተቃራኒውን ሁኔታ የመፍጠር ውጤት ማሳለፋቸውን ወ/ት ብርቱካን ይናገራሉ።

"ሚሌኒየሙ የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ መነቃቃት ፈጥሯል" ሲሉ የሚገልፁት የኢዲአፓ-መድህን ሊቀመንበር አቶ ልደቱ አያሌው፣ ብሔራዊ መግባባትን ለመፍጠር ግን አንድም መድረክ እንዳልተዘጋጀና በዚህ ላይ በሚሌኒየሙ መነቃቃት ተፈጥሯል ብለው እንደማያምኑ ገልፀዋል።

ፕሮፌሠር በየነ ጴጥሮስ በበኩላቸው፤ ምክር ቤቱ ሲቋቋም ብሔራዊ መግባባትን እንደሚፈጥር ዕቅድ ቢይዝም ተፈፃሚ አለመሆኑን ይገልፃሉ። ህዝቡ ረሃብ ላይ መሆኑን ዓለም እየዘገበ ባለበት ሁኔታ ለሚሌኒየሙ የሰጠው ክብር ከእውነቱ ጋር የሚቃረን መሆኑንና ስለሚሌኒየሙ የሚወራው ከገደብ በላይ መሆኑን ተናግረዋል። ፕሮፌሠር በየነ ተተከሉ የተባሉት ችግኞች ፀድቀው ሳይታዩ፣ በህዝብ ታቅፈው የሚራመዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች መግባባት ሳይፈጠርና መነጋገር በማይቻልበት ሁኔታ የሚሌኒየሙ ዓላማ ተሳክቷል ማለት ከእውነት ጋር የማይሄድ ህልም ነው ይላሉ።

የታሪክ ምሁሩ ፕሮፌሠር ባህሩ ዘውዴ 'The challenge of the New Millennium Renaissance or reappraisal? በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ፣ ከሚሌኒየም በዓል አከባበር ጋር በተጓዳኝ ተጠቃሚ ልንሆን የምንችልበትን ዝርዝር ሃሳብ ኢንተር አፍሪካ ግሩፕ ባዘጋጀው ውይይት ላይ አቅርበው ነበር።

የሚሌኒየም በዓሉ የብሔራዊ መግባባት አጀንዳ ትልቅ ትኩረት አግኝቶ፣ ኢትዮጵያ ከድህነት የምትላቀቅበትን ጠንካራ ዲሞክራሲያዊ ሀገር እንድትሆን ጥናታዊ ጽሑፋቸውን ያቀረቡት ፕሮፌሠር ባህሩ ዘውዴ፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ መግባባት እንዴት ሊመጣ ይችላል የሚለውን ወሳኝ ጥያቄ ለመመለስም ሞክረዋል።

በኢትዮጵያ የብሔራዊ መግባባትን ለማስፈን ዋናው ዓላማ፣ የልማት ጋሬጣ የሆኑብንን መሰናክሎች ለማሸነፍ የተሻለች ሀገር መገንባት መሆኑን የሚገልፁት ፕሮፌሠር ባህሩ፣ ኢትዮጵያ ያሉባት ችግሮች ውስብስብ ከመሆናቸው የተነሣ የችግሮቻችን የአፈታት ስልት በአዋጅና ቲያትራዊ በሚመስል የአንድ ደቂቃ ፀሎት ብቻ ሊሆን የማይችል ነው በማለት ያሰምሩበታል።

ፕሮፌሠሩ በኢትዮጵያ ብሔራዊ መግባባት መገንባት የሚቻለው ከልብ የመነጨ የፖለቲካ መቻቻልና የዲሞክራሲን እና የመልካም አስተዳዳር ዘይቤዎች የሚያበረታታና የሚያሳድግ ባህል መፍጠር ሲቻል ነው ይላሉ።

## የሌላ ሀገር ተሞክሮ

የፈረንጆቹን 2000 (ሚሌኒየም) ካከበሩት ሀገራት ውስጥ በአሜሪካን ሀገር ቺጋዮ የሚሌኒየም ፓርክ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ሲሆን፣ እንግሊዛውያን ቢያከብሩ ቢያከብሩ ምሁራኖቻቸው ባደረጉት ሰፊ ክርክር "ዊኒስተን ቸርችልን" የሺህ ዓመቱ ምርጥ በሚል በውይይት ተጨምቆ ከነወጣው ትክክለኛ ታሪካቸው ጋር ለትውልድ አስተላልፈዋል። ሮማውያን ወደ ሚሌኒየማቸው ለመግባት ሦስት ዓመት ሲቀረው ስለሀገራቸው ባደረጉት የተጠናከረ ግምገማ ሀገራቸው ምን እንደነበረች የተጠናና የተረጋገጠ ታሪክ አስቀምጠው በቀጣየስ ለለውጥ ለመነሳት ያለፈውን ስህተቶቻቸው ነቅሰው አውጥተዋል።

## የሚሌኒየም ውጤት

በሥራ አስፈፃሚው ውስጥ የተካተቱት የሀገሪቱ ታላላቅ ባለሥልጣኖች እንደመሆናቸው አዳዲስ ሃሳቦችን አፍልቀው በሀገር ደረጃ ሊያስመሰግን የሚችል ሥራ አልሠሩም።

ከተጀመሩት ፕሮጀክቶች ዋና ዋናዎቹ ቢያንስ በቅርስነት ሊተላለፉ ይችላሉ ተብለው የነበረ ቢሆንም ጭርስኑ አልተጀመሩም።

የሚሌኒየም ምክር ቤቱ ከዋናው ሥራው ይልቅ ለመገናኛ ብዙኀን ሽፋን በተሰጠ ትኩረት የህዝብ ግንኙነት ሥራ ብቻ ነው የሠራው። በተጨማሪም ምክር ቤቱ ከስትራቴጂክ ዕቅዱ ውጪ ቀናትን እያስታከከ በዓል ሲያከብር የሥራ ጊዜውን አባክኗል የሚል አስተያየት አለ።

ምክር ቤቱን በይፋ ለመዝጋት ጥቅምት 8 ቀን ሲሰበሰብ ውጤቱን መዝኖ ያሳውቃል። ምናልባት በዓሉ አከባበሩ ሲጀምር "ኢትዮጵያውያን እጅ ለእጅ ተያይዘን በጋራ ብሔራዊ ስሜት የበለፀገችና ዲሞክራሲያዊት ሀገር ለመገንባት ብሔራዊ ንቅናቄ ተፈጥሮ ማየት" በሚል ያስቀመጠው ራዕይ "ተሳክቷል" ይለን ይሆን?